በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - ክፍል 2


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፦*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ኅዳር 1 ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# <u>ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት</u>

- “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበት የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።” ***<u>ሉቃ 11፡44</u>***
- ቤተ ክርስቲያን (ክርስትና) ስትመሠረት የነበረውን የዓለም ገጽታ በአግባቡ ለመረዳት የአይሁድን፣ የአህዛብንና የፖለቲካ ሁኔታቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

## ***<u>አይሁድ</u>***

1. *<u>የፖለቲካ ሁኔታ</u>*

- ሮማውያን ኢየሩሳሌምን አሸንፈው በ63 ዓ.ዓ. ከተቆጣጠሩ በኋላ አይሁድ በሮማውያን የሚተዳደሩ ሆነው ነበር፡፡
- ሮማውያንም አይሁዳውያን ገዢዎችን በሮማውያን ወኪሎች ሥር በማድረግ ይሾሙ ነበር፡፡

2. *<u>ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወታቸው</u>*

- በርካታዎቹ አይሁድ በድኅነት የሚማቅቁ ሆነው ኑሮአቸውም አሳዛኝ ገጽታ ነበረው፡፡

3. *<u>ሃይማኖታቸው</u>*

- ሕጉን የሚፈጽሙ ባይሆኑም በሙሴ ሕግ ግን ይመሩ ነበር፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

4. ***የአይሁድ ምኩራብ (ሲናጎግ)***

- ምኩራብ ለአይሁድ የሃይማኖታቸውና የማኅበራዊ ሕይወታቸው ማዕከል ነበር፡፡
- እያንዳንዱ ከተማም የራሱ ምኩራብ ነበረው፡፡ ሥፍራውም ለመታጠብና ለመንጻት ሥርዓት ያመች ዘንድ በወንዝ ወይም በባሕር ወይም በውሃ አቅራቢያ ይደረግ ነበር፡፡
- በዘመኑ ኢየሩሳሌም ወደ 400 የሚጠጉ ምኩራቦች ይገኙባት ነበር፡፡ ምኩራብ ከፍ ባለ ሥፍራ ይሠራ ነበር፡፡
- እያንዳንዱ ምኩራብ የየራሱ አለቃ ነበረው፡፡ "ኢየሱስ ግን የተናገሩትን ቃል አድምጦ ለምኵራቡ አለቃ። እመን ብቻ እንጂ አትፍራ አለው።" ***ማር 5፡36፡፡*** ከአለቆቹም ጋር በርካታ የሕዝብ ሽማግሌዎች አንባቢዎችና ተርጓሚዎችም ነበሩ፡፡ በሌላም በኩል ገንዘብ የሚሰበስቡ ለድሆችም የሚያካፍሉና የተለያዩ ሥራዎችን ይሠሩ የነበሩ ይገኙ ነበር፡፡
- በምኩራብ የነበረው የአምልኮት ሥርዓት እጅግ ረጅም ሰዓት የሚወስድ ነበር፡፡ በአምልኮት ሥርዓታቸውም መዝሙረ ዳዊትን በመዘመር ብሉይ ኪዳንንም በማንበብ ይተረጉሙ ነበር፡፡
- መሥዋዕት ግን በኢየሩሳሌም በነበረው ምሥዋዕ (መሠዊያ) ላይ ብቻ የሚቀርብ ነበር፡፡
- መሥዋዕት ማቅረብንም እውነተኛ መሥዋዕት ከሆነው ከጌታችን ከአምላካችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀል በኋላ በመሠዊያቸው መቃጠል የተነሳ ሙሉ በሙሉ አቁመዋል፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

5. ***የአይሁድ ቡድኖች***

- ቤተ ክርስቲያን ስትወለድ በተለያዩ ቡድኖች የተከፈሉ አይሁድ ይገኙ ነበር፡፡
- ዋናዎቹም ቡድኖች ሦስት ነበሩ፡፡ እነርሱም ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያንና እሴዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

ሀ. ***ፈሪሳውያን***

- እነዚህ የተመረጡ ቡድኖች ወግ አጥባቂ ሆነው የሙሴን ሕግና ባሕላችን እንጠብቃለን የሚሉ ነበሩ፡፡

“ጻድቃን እንደ ሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፥ እንዲህ ሲል፦ ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ። ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ። እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ። ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር። እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።” ***ሉቃ 18:9-14፡፡***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## ጻፎች

- **እነዚህም ከፈሪሳውያን ጋር ተጠቅሰዋል፡፡** “በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው። ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል።” ***ማቴ 23:2፡፡***
- “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበት የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።” ***ሉቃ 11:44፡፡***
- **ጻፎች ከፈሪሳውያን ጋር ሆነው መጻሕፍትን የሚያስተምሩ ፈሪሳውያን እንጂ የተለዩ የሃይማኖት ቡድኖች አልነበሩም፡፡**
- **ጻፎች በዚህ መልክ የታወቁት ከዕዝራ ዘመን አንስቶ ነው፡፡** “በያቤጽም የተቀመጡ ***የጸሐፊዎች*** ወገኖች ቲርዓውያን፥ ሺምዓታውያን፥ ሡካታውያን ነበሩ እነዚህ ከሬካብ ቤት አባት ከሐማት የወጡ ቄናውያን ናቸው።” ***ቀዳ ዜና 2:55፡፡***
- **ጻፎች በሕዝቡ ዘንድ ክብር ይሰጣቸው ነበር፡፡**
- **ጌታችን ስለጻፎችና ፈሪሳውያን ከተናገራቸው የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡** “ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።” ***ማቴ 5:20፡፡*** “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ፥ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ።…” ***ማቴ 23:13-…***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

ለ. <u>ሰዱቃውያን</u>

- **በመሠዊያው ከሁሉ በላይ ሥልጣን የነበራቸውና ከመሠዊያው ከሚገኘው ስጦታ ይካፈሉ የነበሩ ቡድኖች ናቸው፡፡**
- **በጣም ሀብታሞች፣ በገንዘብና ቁሳዊ ነገር ብቻ ላይ አትኩሮት የነበራቸው የፈሪሳውያን ጠላቶች ነበሩ፡፡**
- **ሰዱቃውያን በትንሳኤ ሙታን አያምኑም፡፡**
- “ጳውሎስም ሸንጎውን ትኩር ብሎ ተመልክቶ። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ እስከዚች ቀን ድረስ በመልካም ሕሊና ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ኖሬአለሁ አለ። ሊቀ ካህናቱም ሐናንያ አፉን ይመቱት ዘንድ በአጠገቡ ቆመው የነበሩትን አዘዘ። በዚያን ጊዜ ጳውሎስ፡- አንተ በኖራ የተለሰነ ግድግዳ፥ እግዚአብሔር አንተን ይመታ ዘንድ አለው፤ አንተ በሕግ ልትፈርድብኝ ተቀምጠህ ሳለህ ያለ ሕግ እመታ ዘንድ ታዛለህን? አለው። በአጠገቡ የቆሙትም። የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት ትሳደባለህን? አሉት። ጳውሎስም፡- ወንድሞች ሆይ፥ ሊቀ ካህናት መሆኑን ባላውቅ ነው፤ በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትናገር ተብሎ ተጽፎአልና አላቸው። ጳውሎስ ግን እኩሌቶቹ ሰዱቃውያን እኩሌቶቹም ፈሪሳውያን መሆናቸውን አይቶ። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ፈሪሳዊ የፈሪሳዊም ልጅ ነኝ፤ ስለ ተስፋና ስለ ሙታን መነሣት ይፈርዱብኛል ብሎ በሸንጎው ጮኸ። ይህንም ባለ ጊዜ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል ጥል ሆነ ሸንጎውም ተለያየ። ሰዱቃውያን። ትንሣኤም መልአክም መንፈስም የለም የሚሉ ናቸውና፤ ፈሪሳውያን ግን ሁለቱን ያምናሉ። ታላቅ ጩኸትም ሆነ፥ ከፈሪሳውያንም ወገን የሆኑት ጻፎች ተነሥተው። በዚህ ሰው ላይ ምንም ክፉ ነገር አላገኘንበትም፤ መንፈስ ወይስ መልአክ ተናግሮት ይሆን? ብለው ተከራከሩ።” ***<u>የሐ. ሥራ 23፡1-9፡፡</u>***
- **ጌታችን** “ኢየሱስም፡- ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ አላቸው። ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንድትጠበቁ ብዬ ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኋችሁ እንዴት አታስተውሉምን? እነርሱም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት እንጂ ከእንጀራ እርሾ እንዲጠበቁ እንዳላላቸው ያን ጊዜ አስተዋሉ። ” ***<u>ማቴ 16፡6፣ 16፡11-12፡፡</u>***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## ለ. ሰዱቃውያን...

- **ሰዱቃውያን በመላእክት ወይም በመንፈስም መኖር አያምኑም፡፡**
- "ሰዱቃውያን። ትንሣኤም መልአክም መንፈስም የለም የሚሉ ናቸውና፤ ፈሪሳውያን ግን ሁለቱን ያምናሉ።" ***የሐ. ሥራ 23፡8፡፡***

ሐ. **እሴዎች**

- ስለ እሴዎች በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ባይጠቀስም ጌታችን በምድር በተመላለሰበት ዘመን በነበረው ሃይማኖታዊ ሕይወት ተጽዕኖ ያሳድሩ እንደነበር አዳዲስ ጥናቶችና ግኝቶች ጠቁመዋል፡፡
- አንዳንዶች የጌታችን ደቀመዛሙርት ከነዚህ ወገን የተገኙ እንደሆኑም ታውቋል፡፡
- እንደ ፈሪሳውያን በቃል ብቻ ላይ አትኩሮት በማድረግ ሳይሆን ለአይሁድ ሕግ ተገዢ ነበሩ፡፡
- በሃይማኖት  ሕይወት ማስመሰልን በመቃወም መጻሕፍት እንደሚሉትና እንደሚያስተምሩትም ለመኖር ይጣጣሩ ነበር፡፡
- እነዚህ ወገኖች ኩምራን በምትባል ደሴት እንደ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መሲህ የጦር መሪ ሆኖ በመምጣት ነጻ ያወጣናል በማለት በገዳማዊ ሕይወት ተወስነው በመጠባበቅ ይኖሩ ነበር፡፡

6. ***የአይሁድ ጉባኤ - ሲንሃድሪም***

- የአይሁድ ሲኖዶሳቸው - ታላቁ ወሳኝ ጉባኤ ነው፡፡
- ጌታችንና ደቀመዛሙርቱም የተፈረደባቸው በዚሁ ጉባኤ ፊት ነው፡፡ የጉባኤውም አባላት ከ70 እስከ 72 የሚሆኑ ከሦስት ቡድኖች (ሊቃነ ካህናት፡ አገልግሎት ከሚሰጡ ከሃያ አራቱ ሰሙነኞች መካከል የተመረጡ መሪዎች፣ ሽማግሌዎች (የየነገዱ መሪዎች)፣ ጻፎች (የፈሪሳውያን መሪዎች)) የተመረጡ ነበሩ፡፡ "በነጋም ጊዜ የሕዝቡ ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች ጻፎችም ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸው ወሰዱትና፡፡" ***ሉቃ 22፡66፡፡***
- ጉባኤውም በመሠዊያው አጠገብ ይካሄድ ነበር፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *ምን ተማርን?*

1. አይሁድ አምልኮታቸው ከልብ የመነጨ ስላልነበረ ብዙዎቹ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ሳያምኑ ቀርተው መልካሙ ዕድል እንዲያመልጣቸው ሆነዋል፡፡

- እኛም በውጭ እያስመሰልን ለመኖር ሳይሆን በውስጡ ልባችን እግዚአብሔርን ለማመንና ለማምለክ አትኩሮት እናድርግ፡፡

2. አምላካችን ሰው ሆኖ በምድር በተመላለሰ ጊዜ የነበሩ አይሁድ እጅግ ጽንፈኞች ነበሩ፡፡ ይመጣ ዘንድ ይጠብቁት የነበሩት ከሮማውያን ቅኝ ገዢነት ነጻ የሚያወጣቸውና ባለጠጋ የሚያደርጋቸውን መሲሕ ነበር፡፡

- መሲሑም ኢየሱስ ክርስቶስ በፊታቸው ተአምራትን ቢያደርግም የሚፈልጉትን ስላላደረገ የሆነውን ሁሉ በአግባብ የሚመለከቱበት ዕድል አጥተው የሚበዙት በአምላክነቱ ማመን ተሳናቸው፡፡
- እኛም ለሚሆኑ ነገሮች ምቹ መሆን እንደሚገባን (ንስሐ ለመግባት፣ ከኃጢአት ለመለየት…) ትተን ዘንግተን በግትርነት እንዳንኖር እንጠንቀቅ፡፡ "ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፡፡" እንደተባለ፡፡ ***ዕብ 3፡13፡፡***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *አሕዛብ*

- አሕዛብ የእግዚአብሔርን፣ የኃጢአትን፣ ወይም የቅድስናን ትርጉም ወይም ምንነት የማያውቁ ጣዖታትን ያመልኩ የነበሩ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ናቸው፡፡

1. **<u>የአሕዛብ ፍልስፍና</u>**

- **ክርስትና በተመሠረተበት የመጀመሪያ ዓመታት የነበሩት የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች** የኤፊቆሮስና ኢስጦኢኮች ነበሩ፡፡ “ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጦኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ። አንዳንዶቹም። ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል? አሉ፤ ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሣኤውን ወንጌል ስለ ሰበከላቸው። አዲሶችን አማልክት የሚያወራ ይመስላል አሉ።” ***<u>የሐ. ሥራ 17፡18፡፡</u>***
  - ***<u>የኤፊቆሮስ ፈላስፎች፡-</u>*** ሁሉንም ሃይማኖቶች የሚቃወሙ ሲሆኑ በማንኛውም ሃይማኖት ያለ እምነት ሁሉ ኃጢአት ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡
  - **በመላው ዓለም የእግዚአብሔር ሕግ ወይም ሥርዓት የለም፣ ከሕዝብ ተነጥሎ በመኖር ለሕይወጥ መጨነቅ አይገባም ብለው ያስተምራሉ፡፡**
  - **የሚበዙት ሮማውያን በዚህ ፍልስፍና ያምኑ ነበር፡፡**
  - ***<u>የኢስጦኢኮች ፈላስፎች፡-</u>*** በአንድ እግዚአብሔር ያምናሉ፣ ሁሉም የተገኘበት አንድ መንፈስ አለ እያንዳንዱም ሰው ከእግዚአብሔር ጠባይ የወጣ ፍናጣቂ ነው፤ **ሰውም ይህን ፍንጣቂ በመጠበቅ በመልካም ሁኔታ ዘወትር እንዲያበራ ማድረግ ይኖርበታል** ብለው ያምናል፡፡
  - **ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠው ታላቁ ስጦታም አእምሮ ነው ይላሉ፡፡**

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## 2. የአሕዛብ ጠባያት

- **አህዛብን በተሻለ ሁኔታ የሚገልጻቸው *ሮሜ 1:18-32* የተጻፈው ነው፡፡** *"እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ። ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ። እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፥ ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤ እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።"*

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *የሮም መንግሥት*

- የአይሁድ አገሮች ጠንካራ ሆኖ በአግባቡ በተደራጀው በሮማውያን ገዢዎች (መንግሥት) ቁጥጥር ሥር ነበር፡፡ ይህንንም የሮም ገዢዎች ነገር በወንጌላት፣ በሐዋርያት ሥራ ተጽፎ እናነባለን፡፡
- የሮማውያን አገዛዝ በአውሮፓ፣ በእስያና በአፍሪካም ተስፋፍቶ ነበር፡፡ ግዛቱም በምዕራብ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ምስራቅ ቀጥሎም በደቡብ የሜዲትራንያን ውቅያኖስን በመያዝ አፍርካን ያካልላል፡፡
- የሮም መንግሥት በአውራጃዎች የተከፈለ ሆኖ እያንዳንዱም አውራጃ ከዋና ከተማዋ ከሮም የተሰየመ ገዢ ነበረው፡፡ እነዚህም በሮም ሕግና በግብር ሥርዓት የሚተዳደሩ ነበሩ፡፡ ግብጽም በሮም ግዛት ሥር ነበረች፡፡ *ማቴ 27፡21፡፡*
- በዘመኑ የነበረው አገዛዝ የተሸነፉ አገሮች ድል ባደረጓቸው አገሮች ግዛት ሥር እንዲወድቁ የሚያስገድድና የተሸነፉትም በቋሚነት ገንዘብ እየከፈሉ በገዛ አገራቸው ለመኖር እንዲችሉ የሚያደርግ ነበር፡፡
- ሮማውያን በየጊዜው በግዛታቸው ሥር ያለውን የሕዝብ ቁጥር ለማወቅ ቆጠራ ያካሂዱ የነበሩትም በዚሁ የተነሳ ነው፡፡ "በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች።" ***ሉቃ 2፡1፡፡***
-

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## የሮም ዜግነትን የማግኘት መብት

- ይህ ልዩ መብት የሚያሰጥ ዕድል ነበር።
- የሮም የዜግነት መብት በገንዘብ በመግዛት ወይም ለረጅም ዘመናት በውትድርና በማገልገል ለተወሰኑ ሰዎች የሚሰጥ መብት ነበር።
- በዜግነት የሚገኘውም መብት በሕግ ጥላ ሥር ጥበቃ ማግኘት፣ ፍርድ ቤት በመቅረብ ካልተወሰነ በቀር ያለመታሠር መብትና በሮም ፍርድ ቤት የመዳኘት ዕድልን ነበር።
- “ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ፤ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ፥ አሳስሮት ነበርና።” ***የሐ. ሥራ 22:29።***
- “ጳውሎስ ግን። እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኅኒ ጣሉን፤ አሁንም በስውር ይጥሉናልን? አይሆንም ራሳቸው ግን መጥተው ያውጡን አላቸው።” ***የሐ. ሥራ 16:37።***
- “እንግዲህ በድዬ ወይም ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ እንደ ሆነ ከሞት ልዳን አልልም፤ እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደሆነ ግን ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ።” ***የሐ. ሥራ 25:11።***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *ምን ተማርን?*

1. ክርስትና በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የገጠሙት ፈተናዎች ከአይሁድ፣ አህዛብና የሮም መንግሥት የሆኑ ናቸው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና በተለያዩ ሂደቶች የተከሰቱትን ለመረዳት የሚያግዘን ጉዳይ ነው።
2. ክርስትና አቅም ከነበራቸውና በኃይል ከተደራጁ ኃይሎች ታላቅ መሰናክል ገጥሞት ነበር። ነገር ግን በድል አድራጊው በእግዚአብሔር ኃይል ክርስትና ሁሉንም ኃይሎች አሸንፎ በፍጥነት ተስፋፍቷል።
3. ክርስትና እነዚህን አይሁድን፣ አሕዛብንና የሮም ቄሳሮችን ለመዋጋት በመሞከር ወይም በመቃወም ሥራ አልተጠመደም። ነገር ግን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕዝቡን እምነት ያንጽና የእግዚአብሔርንም መንግሥት ይገነባ ነበር እንጂ። ጨለማን ከመክሰስ ይልቅ የሻማን ብርሃን ማብራት የተሸለ ነውና።
4. ዛሬም ባማው ኅብረተሰብ መካከልም በርካታ ተጻራሪ መጥፎ ነገሮች ይገኛሉ። የክርስትናው መንገድ መጥፎ ነገሮችን መክሰስ ሳይሆን ትኩረታችንን እውነተኛ፣ ትክክለኛና ጤናማ በሆኑ ነገሮች ላይ በማድረግ እነዚህን መልካም ነገሮች ማስፋፋት ላይ ነው።

ይቀጥላል…

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org